# ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያንና አፍሪካን በመወከል በፒትስበርግ G-20 ስብሰባ በመገኘታቸው የድጋፍ ሰልፍ ተካሄደ፡፡

በዋሽንግተን፣ በፒትስበርግና በፔንስሊቪኒያ ከተሞች ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያንና አፍሪካን በመወከል በአሜሪካ ፒትስበርግ ከተማ በሚካሄደው የG-20 ሀገሮች ስብሰባ በመገኘታቸው ደስታቸውን በዛሬው ዕለት ባካሄዱት የድጋፍ ሰልፍ ገለፁ፡፡ የኢትዮጵያ አሜሪካ የሲቪል ማህበራት ህብረት በመባል የሚታወቅ ድርጅት ባዘጋጀው በዚህ ሰልፍ የተለያዩ መፈክሮችን ያነገቡና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓለማ የተዋቡ ሰልፈኞች ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያንና አፍሪካን በመወከል የአህጉሪቷን ችግሮችና የወደፊት ተስፋዎች የበለፀጉ አገሮች መሪዎች በትክክል እንዲገነዘቡት እንዲሁም በአፍሪካ አህጉር የሚታዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና የአየር ብክለት ችግሮች የአለም አቀፍ ችግሮች የመፍትሄ አካል እንደሆኑ ለሚያደርጉት ጥበብ የተሞላበት ጥረት ስልፈኞቹ አድናቆታቸውን ገልፀዋል፡፡

በስልፉ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያውያን ከያዟቸው መፈክሮች መካከል «ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አህጉራችን ወክለው በመገኘታቸው እንኮራለን ፣ የኢትዮጵያና የአሜሪካ ወዳጅነት ፀንቶ ይኑር፣ ጠ/ሚኒስትር መለስን እናመሰግናለን ፣ የአፍሪካ አህጉር ድምፅ ይሰማ፣ አለም አቀፍ ሽብርተኝነትና የአሸባሪዎች ከላላ የሆኑ አገሮችን እናወግዛለን» የሚሉ ነበሩ፡፡

በፒትስበርግ ከተማ ከታዩት የተለያዩ አገሮችና ቡድኖች ሰልፎች መካከል ይህን ሰልፍ ልዩ የሚያደርገው ሰልፈኞቹ ኢትዮጵያውያን የጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊንና የፕሬዚዳንት ኦባማን ፎቶግራፍ ምስሎች በጣምራ በመያዝ ሁለቱ መሪዎች ለአፍሪካና ለአሜሪካ የጠነከረ ወዳጅነት ለሚያደርጉት አስተዋፅዖ አድናቆታቸውን መግለፃቸው ነው፡፡